# ወሬ ባናበዛ

(ዓለሙ አሎ)

ለኔም ሆነ ላንተ ላገርም ጥሩ ነው
ወሬ ባናበዛ አሉባልታ ብንተው።

ብዙ ጊዜ አለፈ ወሬ ስንሰልቅ
ከሓሜት ሳንወጣ ካሉባልታ ሳንርቅ
አንተ እኔን ስትንቅ እኔ ባንተ ስስቅ።

ምላስን በማርዘም አፍን በማሞጥሞጥ
እውነታን በመርገጥ ታሪክ በመለመጥ
ከመስመር በመውጣት ሰው ላይ በመናፈጥ
አንችልም ለማምጣት የምንሻውን ለውጥ።

ለመደጋገፉ ለመተጋገዙ
ለሁሉም መልካም ነው አንድ ላይ መጓዙ።
መስማማት ካልቻልን ልዩነት ከሰፋ
ጉልበትና ገንዘብ ጊዜ ሳናጠፋ
ብዙ ሳንጫጫ ፊሽካ ሳንነፋ
እርስ በርስ ተባልተን አጥፍተን ሳንጠፋ
ተለያይተን ብንሄድ እምብዛም አይከፋ።

እንግዲህ ወንድሜ ዕድሜ ጤና ካለን
ከሃሜት እርቀን ካሉባልታ ፀድተን
ምናልባት አንድ ቀን አብረን እንሆናለን።
ግን እስከዛው ድረስ  ወሬ አናብዛ አሁን
እኔ እንደፈለኩት አንተም እንዳሻህ ሁን።
እርስ በርስ አንሁን እንቅፋት ደንቃራ
በመረጠው መንገድ ሁሉም ይሰማራ
በዚም በዛ ብለን ወደ ግቡ እናምራ።

አሉ_አለች ማለት ወሬ ምን ያረጋል
መንገዱ ሰፊ ነው ለሁሉም ይበቃል
ሜዳውም ጫካውም ሁለቱም ያስኬዳል።

ዕባብና ጊንጡን ካልፈሩ ውሃ ጥም
በረሃውም ቢሆን አላስኬድም አይልም።

እኔ ልሂድ በዚ አንተ ቅደም በዛ
ምን አለበት ወንድም ወሬ ባናበዛ።